**ለሌሎች ስም እና የግል መረጃ ተላልፎ እንዲሰጥ - ፈቃድ መስጫ ቅፅ**

(ፊርማ ከሚፈረምበት መሥመር ውጪ ሁሉንም ነገር ይተይቡ ወይም በእጅ ይጻፉ)

**የእርስዎ ስም፡-** ______________________________

**ይህን የአቤቱታ ክስ ፋይል የሚከፍቱበት ትምህርት ቤት ወይም ሌላ ተቋም ስም፡-** ______________________________

---

- ይህ ቅፅ Office for Civil Rights (OCR) (ፀረ-ሲቪል መብቶች መድልዎ ቢሮ) የእርስዎን ስም እና ሌላ የግል መረጃ OCR የእርስዎን አቤቱታ መፍትሔ ለመስጠት ሲባል ከሌሎች ጋር መረጃውን መጋራት አለብኝ ብሎ በሚወስንበት ጊዜ ማጋራት ስለመቻል አለመቻሉ ጥያቄ ያቀርብልዎታል።
- ለምሳሌ፣ አንድ ትምህርት ቤት በአንድ ግለሰብ ላይ በደል መፈጸም አለመፈጸሙን አጣርቶ ለማወቅ ሲል፣ ተጨባጭ እውነታዎችን ለማረጋገጥ ወይም ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ሲባል OCR ብዙውን ጊዜ በደል ደረሰብኝ ያለውን ግለሰብ ስም እና ሌላ የግል መረጃ በዛ ትምህርት ቤት ለሚገኙ ሠራተኞች ሊገልጽላቸው ይገደዳል። OCR ይህን በሚያደርግበት ጊዜ፣ OCR ግለሰቡ ላይ ወይም ከግለሰቡ ጋር ግንኙነት ባላቸው ሰዎች ላይ ማናቸውም ዓይነት የበቀል እርምጃ መውሰድ አጥብቆ የተከለከለ መሆኑን መረጃውን እንዲያውቁት ለሚደረጉት ሠራተኞች በቅድሚያ ያሳውቃቸዋል። OCR በተጨማሪ ከምስክሮች ጋር ቃለመጠይቅ እና ከልዩ ባለሙያዎች ጋር ምክክር በሚያደርግበት ጊዜ የግለሰቡን ስም እና የግል መረጃ እንዲያውቁት ያደርጋል።
- OCR ከላይ በተገለጸው መሠረት የእርስዎን ስም ወይም የግል መረጃ ለሌሎች እንዳይገልጽ ካልተፈቀደለት፣ ትምህርት ቤቱ በእርስዎ ላይ የመድልዎ በደል ስለመፈጸሙ ለማረጋገጥ እና የመፍትሔ እርምጃ ለመውሰድ እንዲችል የእርስዎ ስም ወይም የግል መረጃ ለሌሎች መገለጽ እንዳለበት OCR ካመነበት የእርስዎን አቤቱታ ፋይል OCR እንዲዘጋ ሊወስን ይችላል።

  ማሳሰቢያ፡- ወደ OCR የአቤቱታ ፋይል ካስገቡ፣ የትምህርት ቤቱን ወይም የተቋሙን ስም፣ የእርስዎ አቤቱታ ፋይል የተከፈተበትን ቀን፣ በእርስዎ አቤቱታ ውስጥ የተጠቀሰውን ደረሰ የተባለ በደል ዓይነት፣ ለደረሰብዎት መድልዎ መፍትሔ የተሰጠበትን፣ ውድቅ የተደረገበትን ወይም የተዘጋበትን ቀን፣ OCR ውሳኔ ላይ ለመድረስ እንደምክንያትነት የተጠቀመባቸውን መሠረታዊ ምክንያቶች፣ ወይም ከዚህ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን መረጃዎች ጨምሮ OCR ስለ የእርስዎ አቤቱታ የተወሰነ መረጃ ቆንጽሎ ለፕሬስ ወይም ለሕዝብ ይፋ ሊያደርግ ይችላል። ማናቸውም OCR ለፕሬስ ወይም ለሕዝብ ይፋ የሚያደርገው መረጃ የእርስዎን ወይም እርስዎ አቤቱታ ወክለው ያቀረቡለትን ግለሰብ ስም አይጨምርም።

  ማሳሰቢያ፡- OCR መረጃ ለማግኘት በሚፈልግበት ጊዜ ምላሽ እንዲሰጡት ይፈልጋል። በ OCR የምርመራ እና መፍትሔ የማፈላለግ እንቅስቃሴዎች ወቅት ትብብር ሳያደርጉ መቅረት ያቀረቡት አቤቱታ እንዲዘጋ ያስደርግብዎታል።

### እባክዎ ክፍል A ላይ ወይም ክፍል B ላይ ይፈርሙ (ሁለቱም ላይ መፈረም አይቻልም) እና ቅፁን ወደ OCR መልሰው ይላኩት፡-

- አቤቱታውን የሚያቀርቡት ስለራስዎ ከሆነ፣ እዚህ ቅፅ ላይ መፈረም አለብዎት።
- አቤቱታውን የሚያቀርቡት ሌላ ሰውን ወክለው ከሆነ፣ አቤቱታ የሚቀርብለት ግለሰብ እራሱ እዚህ ቅፅ ላይ መፈረም አለበት።

  **ከላይ የተጠቀሰው የማይመለከታቸው ጉዳዮች፡-** የአቤቱታ ፋይሉ የቀረበው ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች ለሆነ ወይም በሕግ ራሱን ችሎ ለመቅረብ እንደማይችል የተረጋገጠለት ግለሰብ ስም ከሆነ፣ ይህ ቅፅ በግለሰቡ ወላጅ ወይም ሕጋዊ ሞግዚት መፈረም አለበት።
- ከአንድ ነጠላ ግለሰብ ይልቅ ብዙ ሰዎችን የያዘ መደብን ወክለው አቤቱታ እያቀረቡ ያሉ ከሆነ፣ ይህን ቅፅ እራስዎ መፈረም አለብዎት።

A. **እኔ <u>የምሰጠው</u> ፈቃድ የ OCR የምርመራ እና የሕግ ማስከበር እንቅስቃሴዎች እንዲያሳልጥ ማንነቴን OCR ለሌሎች አሳልፎ እንዲገልጥ ነው።**

______________________________ ______________________________

**ፊርማ** **ቀን**

**<u>ወይም</u>**

B. **እኔ <u>በምንም ዓይነት መልኩ</u> የእኔን ማንነት (እና አቤቱታ በእነሱ ስም የማቀርብላቸው የእኔን ዕድሜያቸው ለአካለመጠን ያልደረሱ/በእኔ ከለላ ውስጥ ላሉ) ለሌሎች እንዲሰጥ ለOCR ፈቃድ አልሰጥም።** ይህን በማድረጌ OCR የእኔን የአቤቱታ ፋይል ሊዘጋው እንደሚችል ተረድቼያለሁ።

______________________________ ______________________________

**ፊርማ** **ቀን**

በሐሰት ቃል በመስጠት ወንጀል ሕግ መሠረት እኔ ስሙ ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ሰው እውነት ኣና በትክክል እኔ መሆኔን አረጋግጣለሁ፣ እንዲሁም አቤቱታው የቀረበው ዕድሜው አካለመጠን ባልደረሰ/በሕግ ራሱን ችሎ መቅረብ በማይችል ሰው ስም ከሆነ፣ እኔ የዚህ ግለሰብ ወላጅ ወይም ሕጋዊ ሞግዚት መሆኔን አረጋግጣለሁ። ይህ ቃለመሃላ ማንነታቸው በዚህ ሰነድ ላይ በተገለጹት ሰዎች ላይ ብቻ ተፈጻሚ የሚሆን ሲሆን በአቤቱታው ውስጥ ከቀረቡት ፍሬ ነገሮች ጋር ከማናቸውም ጋር ተያያዥነት የለውም።